# የተቀዋሚን ተቀዋሚ ታጋይ ጀግኖች
# ቁጥር 2

*"አንተ ተንኮልም ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ የዲያብሎስ ልጅ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፣ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? አሁን እንሆ የጌታ እጅበአን ተ ላይ ናት፣ እውርም ትሆናለለህ፣ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም"* **ሐዋሪያውቅዱስ ጳውሎስ ኤልማስ ለተባለ በልቡ ቂምና በቀልን እንዲሁም ተንኮልን ተሸክሞ የሚጓዝና ለሰውም ለእግዚአብሐርም የማይመች ለነበረ ሰው እንደተናገረው::**

**ውድ፣ አንባቢዎች፣ ባለፈው ጊዜ በተመሳሳይ ዕርእስ በጽሐፌ መጀመሪያ ላይ እንዳስቀመጥኩት "*ፖለቲካን ለማሳመር ስለሰው አጉል ጥብቅና መቆም*" እንደምጠላ ሁሉ፥ ለአጉል ጨዋነት መመጻደቂያ፣ ለቃላት ማጣፈጪያ፣ ከቅዱስ ቃሉ ያመቸኛል ብለው ጥቅስን የሚያጠቅሱና፣ ለሀጢያታቸው መሸፈኛ የሚጠቀሙ ሁሉ፣ ለጊዜው የጠቀማቸው ቢመስላቸውም ቆይተው በራሳቸው ክፉ ሥራ ተጠልፈው ሲወድቁ የሚረዱ ቢሆንም፣ ለጊዘው ግን ቢያንስ ከህሊና ፍርድ ነፃ አለመሆናቸውን ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል፤፤**

**ለዛሬ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ፣ ያለፈውን ዕርእሴን ሳለቅ፣ መነሻውንና፣ ምንጬን፣ እንደ ቅዱስሚካኤል፡ ቀኑን በፈረስ፥ ሌሊቱን በሰረገላ፣ ገስግሸ ደራሲውን በማግኘቴ መልሰ ለመስጠት ተገድጃለሁ በማለት፣ ህሊናቸውን ሽጠው የውሽት ሽምጥ ጋልበው፣ "እነሆ! በዓመፃ ተፀነስኩ፣ እናቴም በኃጢያት ወለደችኝ" ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው፥ በአመፃ ተጸንሰው በሓጢያት አንደተወለዱ አሁንም የቁም ሞትን ሞተው፣ ሌላውን ሊገድሉ፣ ሌሊቱን በዘቀዘቀ ትራስ ሲቃዡ፥ ቀኑን ከመሰሎቻቸው ጋራ ተንኮል ሲጎነጉኑ የሚውሉት እንደነ አቶ ሰውዬው (ሰሎሞን ቸርነት) ያሉ የ30 ዓመት የሙት ድርጅት ጠባቂ ጀግኖች፣  ለዓይናችን ጤና ገና ብዙ ያሳዩናል::**

**ክቡር አቶ ሰውዬው (ሰሎሞን ቸርነት)፥ ባለፈው ጽሑፌ "*መከበር በከንፈር ነውና ተው እንከባበር*" ያልኩትን የፍቅር ወሰን ጥሰው ዋና ጸሐፊው ተቀምጬ በደረቅ አበሳ እርጠቡ ይነዳል እንዲሉ፣ የፈረደባቸው ዶ/ር ጌታቸው ላይ ሔደው ፊጥ ሲሉ፣  በማየቴ እጅግ በጣም፣ አዘንኩ:: እሰከ አሁን ከነማን ጋራ የእርኩሱን የፖለቲካ ቁርባን እንደበላሁ ሳስበው ደግሞ፣ አሁንም በእዚሁ ቤት የሉሐ! የሉሔ! እያሉ ለጉንጭ ማልፊያ ፖለቲካ፣ የሚሰግዱትን፣ አምላክ ሆይ የሚያደርጉትን አላወቁምና፣ ይቅር በላቸው አልኩኝ::**

**አቶ ሰውዬው (ሰሎሞን ቸርነት)! እርስዎ የተጠቀሙበትን አባባል ልዋስና፥ ዛሬ ገኃድ አውጥተው፥ ፀሐይ እንዲሞቀው ያደረጉልን ነገር ቢኖር፥ እርስዎንና እርስዎን የመሳሰሉት የትግል ኃዋሪያ ነን፥ ከእኛ ወዲያ አገርና ሕዝብ ወዳድ ለአሳር ነው! የሚሉን፣ ወደ ድርጅቱ ግቡ ተብለው ሲጠየቁ ኳሮ ኳሮ፣ ለፍኖተና ለመሳሰሉት ገንዘብ አውጡ ሲባሉ ለወራት ከዓይን የሚሰወሩ የትግል ሊቆች፡ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ" እንዲሉ፣ የኢሕአፓ የቁርጥ ቀን ደራሾች በመሆን ሙት እንዳዬ አሞራ ከኮምፒተር ጀርባ በመሆን አንዴ በብዕር ሌላ ጊዜ በማይክራፎን ማላዘናቸውን እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ የሚያቆሙ አይመስሉም:: ይህም አሁን የተጀመረ አይደለም:: ለዘመናት ወያኔን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ አሽቀንጥሮ ለመጣል ከዋሽንግተን ዲሲና**

ከፓሪስ የተሰራ ዘመናዊ ሪሞት ኮንትሮላቸው ስለሆነ ነው::

በተለይ እርስዎና መሰሎችዎ እየሰራችሁት ያለው በጣም አሳዛኝ ኃቅ የጎደለው አስመሳይ ውንጀላና፣ ኢሕአፓ ከተከፈለ ወዲህ ገሐድ እየሆነ የመጣው አስደንጋጭ ነገር፣ አምነናቸውና ለኢትዮጵያችን ብቸኛ መሪዎች ናቸው ብለን ስንከተላቸው የኖርነው፡ ባለፉበትና በዋሉበት የትግል ሜዳ፡ በሐሰት ስንቶችን ንጹኃን ጓዶቻችን እንደ ወያኔ እንደበሉ መገመት አያዳግትም::

አቶ ሰውዬው (ሰሎሞን ችረነት) ደግሞ፥ በዚህ አያያዝዎ ወይም አቋዋምዎ "አብዩት ልጆቿን ትበላለች" እንደማይሉኝ እርገጠኛ አይደለሁም::

አቶ ሰውየው (ሰሎሞን ቸርነት)ም ሆኑ መሰሎቹ፣ አሁንም ከአንዱ ዕራስ ወርዳችሁ፣ ሳይሆንላችሁና መላ ምታችሁ ሳይሰራ ሲቀር፣ እንደገና ከሌላው ዕራስ ላይ ፊጥ የማለት ባህሪ የተጠናወጣችሁ፣ ለደቂቃ እንኳ ቆም ብላችሁ፣ ራሳችሁን ማየት ብትችሉ ኖሮ፥ አታውቁትም እንጂ!! አምላካችሁንና፣ ወገናችሁን ማቅ ለብሳችሁ ወደንስኃ ቤት ይቅርታ ለመጠዬቅ በወረዳችሁ ነበር::

ምንም እንኳ አናንተ ባለፋችሁት ያለፍኩ የዝያ ጀግና ትውልድ አካል ብሆንም፣ በኢሕአፓ ውስጥ በተፈጠረው የብተና ዘመቻም ሆነ የጥፋት ተልኮ፣ የማልከሰስና የማልወቀስ ተራ የታዳጊ ወጣት ተጋዳይ የነበርኩ፥ የአስራ ስምንተኛ ዓመቴን ዶካ በምትባል ከእምራኩባ አጠገብ በምትገኝ የሱዳን አነስተኛ ከተማ በባቄላ ንፍሮ (ፉል) ያከበርኩ የአሁኑ ጎልማሳ መሆኔን ጠንቅቃ ችሁ ልታውቁልኝ ይገባል:: ስለሆነም፣ በድርጅቱ ውስጥ የማያቸውን ምግባረ ብልሹዎችና፣ ቀቢፀ ተስፋ ሰጪዎችን ደፍሬ ለመናገር ንጹህ ህሊና ያለኝ ሰው መሆኔን አጥብቄ ላሰምርበት እውዳለሁ::

ይሔን ጽሑፍ ለማንበብ እድሉ ያጋጠማችሁ ወገኖች፥ ልትታዘዘቡት የሚገባችሁ ነገር ቢኖር ያ የ1960 ዎቹ ቆራጥ ጀግና ትውልድ ወገኑን ከብዝበዛ ቀንበር አላቆ አገሩን በአዲስ ስርዓት ለመገንባት፣ በሰላሙ አልሳካለት ሲል ለውጥ ነጣቂውን ፋሽስት ደርግ በትጥቅ ትግል ለማርበድበድ ቆራጥነቱን ያሳየበትና በትጥቅ ትግል ታሪካችን እንደ እየሩሳሌም በምንቆጥራት አሲምባ ስም፥ መነጋገሪያ ሳይበርና ድህረ ገጽ ከፍተው "ሙት ይዞ ይሞታል" እንዲሉ ሙሉ ሰዓታቸውን የሚያጠፉት፣ ከእነሱ በተሻለ መልኩ ለሕዝብ ቀረቤታ ይኖረዋል ብለው ባሰቡት የፖለቲካ ድርጅት ላይ ሁሉ ነው::

ውድ ወገኖች፥ ይህ በህዳር መጨረሻ በአብዛኛው አባላቱ ተወግዞ የተገለለው ለውጥ አጋች የኢሕአፓ አካል ከተወገዘው ወንጅል ውስጥ አንዱ፥ ወያኔን ለመታገልና የኢትዮጵያን ህዝብ ለመታደግ ከመታገል ይልቅ ሙሉ ሰዓቱን ሙሉ ኃይሉን የሚያጠፋው ሊታገሉ ከፊቱ የቆሙትን ለማዳከም ከቻለም ለማጥፋት ነው፥ የሚል ነበር::

አሁንም ይሔ ቡድን ሃያ አራት ሰዓት እያጠፋ ያለው፡ በቅድሚያ ይሔን አድራጎቱን ኮንኖ የወጣውን አካል ቀፍድዶ በመያዝና ቃል በገባው መሰረት ለውጥ እንደአያሳይ፡ በእልህም ከሱው ጋር ጦርነት ከፍቶ ሌላ የተቀዋሚን ተቃዋሚ ታጋይ ጀግና መፍጠርን ነው::

እስኪ ለትዝብት አሲምባን ድሕረ ገጽና ፓልቶክ፡ እንዲሁም ደብተራውን ድሕረ ገጽ ተመልከቱልኝ:: በስድብ ፖለቲካ የቀሰሱ ፈጽሞ ትውልዱን ለማራራቅና አጥፍተው

ሊጠፉ የተጠራቀሙ ተሰፋ ቢሶች፡ መሆናቸውን ለመገመት የማንንም ማብራሪያ አያሻም።

ሌላው፡ እንድ በአይምሮየ ውስጥ እየወጣና እየወረደ፡ የሚያስጨንቀኝ ነገር ቢኖር፡ ያ የለውጥ ኃዋርያ፤ የታግሎ ማታገልንና ታግሎ ራስን ነፃ የማውጣትን፡ እንዲሁም የእምቢ አሻፈረኝ አልገዛም ባይነትን፤ በር የከፈተ ጀግና ትውልድ፤ ታሪክ ጊዜ እየረዘመ ዘመን እያስቆጠረ በሔደ ቁጥር፡ ዋጋነቱን እያጣ ተጋድሎው አፈር አየለበሰ፡ በየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ያለፈ ያ ትውልድ አንድ አይነት ባሕሪ አለው ከሚለው መደም ደሚያ ላይ እየደረስኩ የመጣሁበት ወቅት ላይ መድረሴ ነው።  ለዚህም መደምደሚያ ካደረሱኝ ምክንያቶቹ፤ ለዛሬ ጥቂቱችን ልጥቀስ፥

አመሰራረቱና ታሪኩ ኢትዮጵያዊ ባሕሪ ባይኖረውም ለምኒሊክ ቤተመንግስት ያደረሰውን ሎተሪ ተጠቅሞ ኤርትራን አስገንጥሎ ያለ ባሕር በር በተውሶ ወደብ ከውጭ የንግድ ቁሳቁሶችን ለማግኘት የምትፈራገጥ ደካማ ኢትዮጵያን በመግዛት ኢትዮጵያዊ ሳይሆን በውጭው ዓለም ኢትዮጵያዊ እንዲባል አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሕዝብም፤ አገርም፤ ታሪክም እየገደለ ያለው የሰይጣኑ ትንቡሽት ወያኔ ሲሆን።

በሌላ መልኩ፥ በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረውን በፖለቲካ ታሪኩ ከዚሁ ከእኩዩ ወያኔ ታሪክ ጋር በተጓዳኝ ዘመናትን እያስቆጠረ ካለው ለውጥ አጋቹ ኢሕአፓ ጋር ያለው እጅግ ተመሳሳይ ባህሪ ነው።

ለምሳሌ፥

1. ከተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በልዩነት አብሮ ከመስራት ይልቅ፥ የሚቃወሟቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ቢችሉ ለማጥፋት ካልቻሉ ለማዳከም መጣር።

2. ለወደፊት የሚያሰጓቸውን በተለያየ እርከን ያሉ መሪወችን ወይም በጣም ታዋቂ የሆኑ አባሎቻቸውን እውነተኛ ባልሆነ አሉባልታ የሞራል ጥቃት ዘመቻ በመክፈት ማዳካም።

3. የውሰጠ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ብለሹነታቸው። በውስጣቸው የሚነሱትን የድርጅት ለውጥና እድገት ጥያቄዎች፡ በአግባቡ ከማስተናገድና ከመለወጥ ይልቅ፡ ለውጥ ጠያቂውን ማሳደድ፥ በሻጥር ከድርጅቱ ማስወገድ፥ አመች ከሆነላቸውም እስከ ግድላት ድረስ በመሔድ እርምጃ መውሰድ።

4. የሲቪክና የሙያ ማህበራትን፤ ቢችሉ በራሳችው አካልና አምሳል ለመሳል፤ ካልቻሉ ግን እንደ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ማሳደድና ማጥፋት።

5. በጣም አደገኛ የሆነው አፍቃሪ ኢትዩጵያ የተባለወም፡ ኢትዮጵያዊ ባህሪ የለውም የምንለውም አንድ አይነት አስደንጋጭ አካሔድ ደግም፡ "አህያ የሌለው፤ በቅሎ ይንቃል" እንዲሉ፡ ከየአቅጣጨው ምሁራንን በተላያዬ መልኩ ማሳደዱ ላይ የሚያደርጉት የጥፋት ዘመቻ ነው። ሁሉም ዜጋ እኩል ተክለለ ሰውነት ቢኖረውም፡ ለሐገር እድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትን ስልጡን ኃይል ሙህሮቻችን ማጣጣልና በተላያዬ መልኩ በማሳደድ፤ ሁለቱም የፖለቲካ ድርጅቶች አገራዊ ኃላፊነት የጎደላቸው ለፖለቲካ ጥቅማቸው በደንባራ ፈረስ የሚጋልቡ ትእቢተኞች መሆናቸውን ያሳየናል።

6.	ሌላው አሳዛኝ ጉዳይ ደግሞ÷ ያን ያለፈውን ጀግና ትውልድ በተቃራኒው አቅጣጫ እንዲታይ፡ አዲሱም ትውልድ እንዳይቀላቀለው የጥል ግድግዳ ሆኖ ይከልለዋል የምለው አደገኛ አቅጣጫ ነው:: ይህም በአካሔድ እና በአቋም ያለተስማማውን ለማጥቃት፡ የሐሰት ማስረጃ ዶኩሜንት ማዘጋጀቱ ላይ ነው:: ለምሳሌ÷ወያኔ ዶ/ር አስራትን በእስር አማቅቆ ለመግደል÷ ቅንጅትን ከፖለቲካው ጨዋታ ለመስወገድና ወደ እስር ቤት ለመወርወር የተጠቀመውም ይሁን ጠላት የሚላቸውን ለማጥፋት የሚጠቀመው የሐሰት መረጃ ደኩሜንቶችን በካድሬዎቹ በማጻፍ ነው::

ለውጥ አጋቹ ኢሕአፓ ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ እዬተጠቀመ ያለው ነገር ቢኖር፤-ካለ መርሻ ዮሴፍ የአመራር ተሳትፎ አይኔም ጨለማ÷ ጉልበቴም ቄጤማ፤ ነው፤ እያለ በየጉባኤው ድንጋይ የመሸከሙን ያክል መንታ መንታውን እያነባና እየተማጸነ ሲያስመርጣችው የነበረ ቡድን፤ በትግል አያያዙ ላይ ከሱው ጋር ሊቀጥል ባለመቻሉ ብቻ፤  ሰሞኑን የሚያደርገው የሃስት የፖልቶክ ቱልቱላና በአሲምባ ድሕረ ገጽ የሚደረደረው የፈጠራ ክስ እውነት ካማንም ጋር ሳትቆም ፊቷን ዞራለች የሚያሰኝ ይመስላል::

ሌላው የሰሞኑ አስቂኙ የህፃን ጨዋታ ደግሞ÷ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት ተፃፈ የሚሉት ጽሑፍ ነው::  የጸሐፊውን ማንነት 99 ቃልቻ አስጠንቁለው የፀሐፊውን ስም ለባላጋራችው እንደ ነበልባል በብሰለቱና በፖለቲካዊ አመለካከቱ ለሚፈሩት ዶ/ር ጌታቸው ለጥፈው የሚያኾጎደጉዱት ክስ፡ ከሙት ሙቱ ከወያኔ ጋራ ተጓተቱ ለሚሉን የፖለቲካ ቃጭል አቃጫዮች በሩን ቧ አድርጎ አየከፈተ ያለ ያልታደል ቡድን ሆኖ እያየነው ነው::

በማጠቃለያዬ ማለት የምፈልጋው ነገር ቢኖር÷ በአሁኑ ሰዓት ከለውጥ አጋቹ ኢሕአፓ አካል እራሱን ያፀዳው ኢሕአፓ ዲሞክራሲያዊና ከወያኔ ሳምባ ውጭ የሚተነፍሱ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር ዘርዘሬ ካስቀመጥኳቸውና ተመሳሳይ ጥፋቶች ታቅበው፤ እርስ በርስ ከመጠላለፍና ከመተቻቸት ይልቅ ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ የራስን ሰራ ሰርቶ በሕዝብ ዘንድ ታማኝነትን እንዲያተርፉ ሲሆን፤ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የግድ ከሚለው ውጭ፤ እርስ በርሰ ከሞፈካከር ይልቅ ለሰላምና ለዲሞክራሲያው ስርዓት ምቹ ጎዳና ለመጥረግ ቅድሚያ ሰጥቶ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች በሰላም የሚያቀራቁስ ሜዳ ማሰጋጀቱ ላይ ካልተተኮረ በስተቀር÷ ያወቅን መስለን አለማወቀችንን÷ ፖለቲከኞች ስንመስል ውስጣችን እንደቆርቆሮ የሚጮህ ባዶዎች መሆናችንን÷ ብቻ ነው በተግባራችን የምናስመሰክረው::

ከዚህ በመለስ ለአንባቢያን የማስገነዝበው ነገር ቢኖር ደግሞ፤ ወያኔም ሆኑ ለውጥ አጋቹ የኢሕአፓ ቡድን በአሁኑ ሰዓት እያደረጉ ያለው፡ ተመሳሳይ ባሕሪ፡ ውሸት ሲደጋገም እውነትይሆናል የሚለውን ፈሊጥ በመከተል፡ ህ/ሰቡን ሊደርሱ በሚመቻቸው አጋጠሚ ሁሉ በኃስት የቀደማቸውን ጠልፎ በመጣል ለውጥ አጋቹ ኢህአፓ ከፓሪስና ከዋሽንግተን ሆኖ፡ ተንጠባጥበው፤ ተንጠባጠበው፤ በቀሩት አባሎቹ መዋጮ የወረቀት ነብር ሆኖ መቀጠልን÷ ወያኔም ደግሞ ጥረስ ያላቸው ፖለቲከኞች ብቅ ሲሉ ወደ ቃልቲ÷ ሲያነጥሰው አይናቸው ስለሱ የሚያነባውን ወደ ፖለቲካ መሳለቂያው ሜዳ እያስገባ፡ ሌላ አስራ ሰባት ዓመት
ማጃጃሉን ነው::

ስለዚህም ማንም ኢትዮጵያዊ ካረጀና ካፈጀ የፖለቲካ ቂመኛነት ተላቆ፤ የተወሳሰበውን የፖለቲካ ቋጠሮ አላልቶ፡ ለዚህ የማያመቹትን ኮንኖ የራሱን አገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነት

አንዲወጣ አገር ብለው÷ ወገን ብለው÷ በዓላማቸው ፀንተው እንደ ሐዋሪያው ጵውሎስ ተዘቅዝቀው ስቃይን በቁም ከፍለው ህይወታቸውን መስዋዕት ባደረጉ ንጹኃን የኢትዮጵያ የቁርጥቀን ልጆች ስም እማፀናለሁ።

ጉልላት!

hailugt@att.net